የኢሕአፓ የፖለቲካ መመሪያ
የኢሕአፓ የኢኮኖሚ ፖሊሲ
የኢሕአፓ የትምሕርት ፖሊሲ
የኢሕአፓ ፌድራላዊ/የፌድራል ፖሊሲ
የኢሕአፓ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ
ኢሕአፓና የኢትዮጵያ የመከላከያ ፖሊሲ

# የትዝብት አድማስ

የኢሕአፓ የፖለቲካ መመሪያ
የኢሕአፓ የኢኮኖሚ ፖሊሲ
የኢሕአፓ የትምሕርት ፖሊሲ
የኢሕአፓ ፌድራላዊ/የፌድራል ፖሊሲ
የኢሕአፓ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ
ኢሕአፓና የኢትዮጵያ የመከላከያ ፖሊሲ

ፓኖራማ ቁጥር 89

የትዝብት አድማስ

ሚያዝያ 8 ቀን 2002 ዓም

## ሶሻል ዲሞክራሲ

## የኢሕአፓ የፖለቲካ መመሪያ

ፓርቲው በ1976 ዓም ባካሄደው ሁለተኛ ጉባዔ ላይ ካስተላለፋቸው መሠረታዊ ውሳኔዎች መካከል ዋናው የድርጅቱን የፖለቲካ መመሪያ በጥሞና መርምሮ መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ ነበር። ፖለቲካ መርሆዎቹን፥ ከተጨባጩ ሁኔታና ተመክሮውምጋር በመጣጣም ለማሻሻልም ምክንያት ያደረገው ፥ የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታዎችን በሚገባ አጢኖ በደረሰበት ግንዛቤ ነው ።ይህም መሻሻልና ለውጥ በፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራም ሰነድ ላይ በዝርዝር ለሰፈሩት የሀገራችን ዋና ዋና ብሄራዊ ፖሊሲዎቹም መሠረት ነው ። ስለሆነም ፥ እነኝህ ዋና ዋና ፖሊሲዎች የፓርቲውን የፖለቲካ ርዕዮት የሚያንፀባርቁ ናቸው። ጊዜውን ጠብቆም የሶሻል ዲሞክራሲ ርዕዮት የፓርቲው የፖለቲካ መመሪያ እንዲሆን ያስፈለገበትም መሠረታዊ ምክንያት ፥ ለሀገራችን ሁለንተናዊም ሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎች ተገቢና ተስማሚ ይሆናል ተብሎ ስለታመነበት ነው ። ስር የሰደዱና ውስብስብ የሆኑት የሀገራችን ችግሮች በየፈርጃቸው እየተለዩ በሂደት ሊቀረፈቱ የሚችሉት፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የቅርብ ፥የመካከለኛና የሩቅ ጥቅም አንጻር ታይተው፥ ሁነኛ ቦታና ቁርጠኛ ውሳኔ እንዲያገኙ ሲደረግ ነው ። የኢትዮጵያን የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች በአስተማማኝ ደረጃ እየቀረፈ ፥ በቀጣይነት የልማቱን እርምጃ እያከናወኑ፥ የሀገሪቱን ዕድገቱ ለማፋጠን ካስፈለገ ፥ ይህ የሶሻል ዲሞክራሲ የፖለቲካ መመሪያ ማዕከላዊ ሚና ይጫወታል ። ለዚህም ሦስት ዓይነተኛ የልማት ረድፎችን በዕቅድ ውስጥ በማስገባት መንቀሳቀስ እንደሚገባ የምንፈልገው ፥ ለሀገራችን ያለንን ሩቅ ራዕይ አሻግረን በማየት ነው ። ሀገሪቱን ከድኅነት አረንቋ ለማስወጣት ጤናማ የሆነ ማንኛው ዜጋ ሁሉ ኀብረተ -ሱታፌ የሚያደርግበት የብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ድርሻ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ይህን ስንል፥ የግል ሃብት የማፍረት ነፃነት፥ የዜግነት መብት ብቻም ሳይሆን የሕግ ዋስትና ያለው መሆኑንም ጭምር የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫው ነው የሚለው አመለካከት

ዕምነታችን ስለሆነ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ የመድበለ- ፓርቲ የፖለቲካ ህይወት ለሕዝባችን ፍቱን መድኀኒት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ለዕድገታችን አስተማማኝና ለዕርምጃችን ፍጥነት ማረጋገጫ ሊሆን የሚችለው፥ የኢኮኖሚውና የማኅበራዊው ኑሮ መስክ የተለየ ትኩረት ሲሰጠው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም ፡፡ የሀገራችን ድኅነትና ኋላ ቀርነት ዓለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ብቻ ሳይሆን ፥ የዘወትር ኑሯችን መስታወትም ስለሆነ ያንኑ መደጋገም ዕርግጥ ውሀ መውቀጥ ይሆንብናል ፡፡ የኛ የፖለቲካ መመሪያ ሶሻል ዴሞክራሲ እንዲሆን የመረጥነውም፥ለኢኮኖሚው ችግርም ሆነ ለማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ ተቀዳሚ አጀንዳ ለመስጠት ይረዳል በሚል ዕምነት ነው ፡፡

በዛሪይቱ ኢትዮጵያ አስራ አራቱ ሚሊዮን ወጣት በመላው የሀገሪቱ ግዛት በሥራ አጥነት ተቀይዶ ይኖራል፡፡ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ ብቻ አራት መቶ ሽ ያህል ወጣት ትውልድ እንደዚሁ በሥራ-አልባነት እየተንከራተተ ይገኛል ፡፡ ታዲያ የዚህ አፍለኛና አምራች ኀይል ሥራ- ፈት ሆኖ መቀመጥ፥ በመላ ሀገሪቱ ላይ የሚያስከትለውን የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ ለመገደብ ምን ያህል ችግር እንደሆነ መገመት አያስቸግርም ፡፡ በአንድ ሀገር ላይ ሥር የሰደደ የኢኮኖሚ ችግር ፥ በነዋሪዎቹ ዘንድ የሚያመጣውን የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስና የሚያስከትለውንም ማዕበል አስቀድሞ ሊገነዘብ የሚችል መንግሥት ከሌለ ፥ የኋላ ኋላ በሀገሪቱ ላይ ሕዝባዊ አመፅ ማስከተሉ የሚቀር አይሆንም ፡፡ ለሚመጣው ጉዳትና ጥፋት አስቀድሞ ብሔራዊ መከላከያ የማያሰናዳ ሥርዓት፥ የሚኖረው የመጨረሻ ምርጫ፥ አጥፍቶ መጥፋት ብቻ ይሆናል፡፡ የወያኔዎቹ ወዳጆችና የቅርብ አማካሪዎች ይህንን ሁሉ ተገንዘብው ለነመለስ መልካም ምክር ይለግሳሉ ባይባልም ፥ ለራሳቸው ጥቅም ብቻ እንኳን ሲሉ የሚበጃቸውን ማድረግ በተገባ ነበር፡፡ ታሪክ እንደሚያስረዳን ከሆነ ግን ይህንን ያደርጋሉ ተብለው አይጠበቁም፡፡ ሌላ አገልጋይ ፈረስ ለመለወጥ ግን ምናልባት ያስቡ ይሆናል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ምን ጊዜም ቢሆን ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር ፥ የሀገራችንን ችግር ልንፈታው የምንችለው እኛው እራሳችን ብቻ መሆኑን ነው ፡፡ እኛ ልንፈታው ያልቻልነውን ብሔራዊ ችግር፥ባዕዳን ኀይል ይፈቱልናል ብሎ መጠበቅ ፥ ቢያንስ የባዕዳንን ፍላጎትና ዓላማ አለመረዳት ይሆንብናል፡፡ ኢሕአፓ፥ ሶሻል ዴሞክራሲ የፖለቲካው መመሪያ ሊሆን ይገባል ብሎ የመረጠው፥ የሀገራችንን ታሪክ፥ ባኅል፥ የሕዝቡንም ዕምነትና ባኅርይ ፥እንዲሁም፥ የኑሮ ሁኔታ በግምት በማስገባት ነው ፡፡ ሶሻል ዴሞክራሲ ፥ በካፒታሊስቱ ሥርዓትና በሶሻሊዝም ሥርዓት መካከል ያለ ርዕዮት መሆኑ ባይካድም፥ በፖለቲካው መስክ ግን የላብ አደር አምባገነንነት የሚለውን ዕንሰ ሀሳብ አይቀበልም ፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ በተግባር በሚተረጎምበት ሀገር ደግሞ የአምባገነን ሥርዓት ሊከሰት የሚችልበት ዕድል የመነመነ ይሆናል፡፡ ይኸም የሚሆነው ፥ የሀገሪቱ ሕዝብ የሥልጣን ሉዓላዊነትና የህግም የበላይነት ሲረጋገጥ ነው ብለን ማመን አለብን ፡፡ እንደ ካፒታሊስቱ ሥርዓት ግን፥ ሶሻል

ዴሞክራሲ የብዙሃን ፓርቲዎች ዴሞክራሲ ሥርዓትን የሚያምንና የሚከተል ነው ። በኢኮኖሚው መስክ ያለው ዕምነት ፥ በገበያ ላይ የተመሰረተ የውድድር አኮኖሚ ሥርዓት ቢሆንም፥ የገበያ ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ያሟላል የሚል ዕምነት የለውም። እንዲያውም፥ የገበያ ኢኮኖሚ ፥ ፍትኃዊ ያልሆኑና እኩልነት የጎደላቸው ሁኔታዎችን ይፈጥራል ብሎ ይሰጋል ። የሶሻል ዴሞክራሲ የፖለቲካ ሥርዓት መስፈን ፥ ኅብረተሰቡ በኢኮኖሚና በሶሻል ( ማኅበራዊ መስክ ) መስኮች መንግሥት የተለያዩ ርምጃዎችን በመውሰድ እኩልነትና ፍትኅ-ርትዕ እንዲረጋገጡ የሚያስችለው ሥርዓት ነው ። አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ከገበያ ኢኮኖሚ በዕርግጠኝነት ሊያገኝ የማይቸለው አገልግሎት መንግሥት የሚያሟላበት ሥርዓት ነው።

በኢኮኖሚክ መስክ ፥የሶሻል ዲሞክራሲ መሠረታዊ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን የሚከተል ቢሆንም፥ ጠቅላላ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለግል ባለሀብቶች በመተው ፥ሊሟሉ የማይችሉ የኢኮኖሚ ተግባራትን ያከናውናል። አውራ መንገዶችን፥ታላላቅ ድልድዮችን፥ የአይሮፕላን ማረፊያዎችን፥ ወደቦችን፥የከተማ ሆኑ የገጠር በቡር መስመሮችን፥ የፖስታ- ቴሌፎን - ቴሌኮሙኒካሽን ፥ የመገናኛና የታላላቅ መጓጓዥ አገልግሎቶችን ፥ ለርሻና ኢንዱስትሪ የሚውሉ ፕሮጀክቶች ወዘተ መንግሥት እንዲያሟላ ያደርጋል ። የግል ባለሀብቶች ፥ ኮባንያዎችና መንግሥት የሚያከናዉኗቸው ተግባራት በየርከኑ ተለይተው በሥራ ሊወሉ ይገባቸዋል። ይህም ማለት፥ ከትርፋማነት ማነስ የተነሳ የግል ባለሀብቶች ለማምረት የማይፈልጓቸው፥ ነገር ግን ኅብረተሰቡ የሚፈልጋቸው የፋብሪካ ውጤቶችም ሆኑ ሌሎች አግልግሎቶች ካሉ መንግሥት ፋብሪካዎችን አቋቁሞና አምርቶ ኅብረተስቡ እንዲጠቅም ያደርጋል ። ለምሳሌ እንደ መድኅን ድርጅት ( ኢንሹራንስ ) የሕክምና መሳሪያዎች እንደአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

በሶሻል መስክ ያሉ አገልግሎቶች ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲዳረስ ይደረጋል ። ለምሳሌ በጤና በኩል የግል ባለሀብቶችና ባለሙያዎች ሆስፒታልና ክሊኒክ አቋቁመው ለአገልግሎታቸው ዋጋ እያስከፈሉ የጤና አገልግሎት ለማድረግ የሚፈቀድላቸው ቢሆንም፥ መንግሥት፥ የጤና አግልግሎት ለሁሉም ዜጋ መዳረሱን ማረጋገጥ አለበት። ሆስፒታሎችን ክሊኒኮችን በማቋቋም፥ ሐኪሞችንና ሌሎች የጤና ባለሙያዎችን በማሰማራት በተቻለው መጠን አብዛኛው ሕዝብ ያለክፍያ የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል ። የግል የትምህርት ተቋማት አገልግሎታቸውን መስጠታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ትምህርት ለማነኛውም የሀገሪቱ ሕፃናት በነፃ እንዲዳረስ ማድረግ የመንግሥት ኃላፊነት ይሆናል ። የከፍተኛ ትምህርት ለመማር አቅሙም ሆነ ዕድሉ ለሌላቸው ዜጎች ይህ ዕድል እንዳይነፈጋቸው ማድረግ የመንግሥት የማያቋርጥ ጥረትና ኃላፊነት ነው ።በግል የተቋቋሙ

የገንዘብ ተቋማት ፥ ( የፋይናንስ ኢንስትቲውሽን ) ኅብረተሰቡን እንዳይበዘበዙ የቁጥጥር ፖሊሲ ማውጣት የመንግሥት ተግባርና ኃላፊነት ይሆናል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍም ሆነ ጉድለቶችን ለማሟላት መንግሥት የተለያዩ ተግባራትን፥ በግል ባለሀብቶች ምትክ ያከናውናል ። የሠራተኛውን መብት ለማስከበር ፖሊሲ የማውጣት ኃላፊነት የመንግሥት ነው ። የሶሻል ዴሞክራሲ ዓይነተኛ ዓላማና ተግባር ፥ ረዳትና ጧሪ ለሌላቸው አረጋውያን ፥ህሙማን፥ ያለአሳዳጊ ለቀሩ ሕፃናት፥ ለሴቶች፥ ለአካልና ለአዕምሮ በሽተኞች አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ይሆናል ። ከዚህም በቀር የሀገሪቱ ዜጎች የረሀብ ፥ የበሽታና የዕርዛት ሰለባዎች እንዳይሆኑ መከላከልና ሁኔታው ሲከሰትም፥ ፈጥኖ የማስወገድ ኃላፊነት እንዳለበት መንግሥትና ቀሪው ዜጋ ሊገነዘበው ይገባል።

ሶሻል ዴሞክራሲ ስንል ለብዙሃኑ የሚሆን ዴሞከራሲና ሥርዓት ማለታችን ነው። ጠቂቶች ብዙሃኑን የሚበዘብዙበትሥርዓትንም ይቃወማል ። የኢሕአፓ መሠረታዊ ዓላማ ደግሞ ለቡዘሀኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና ዓላማ መታገል ነው። ለዚህም ነው በሶሻል ዴሞክራሲ መርህ መሠረት የሚታገለው።

ፓኖራማ ቁጥር 85

የትዝብት አድማስ

ጥር 26 ቀን 2002 ዓ ም

<u>የኢሕአፓ ኤኮኖሚ ፖሊሲ</u>

ሀገራችን ኢትዮጵያ በድኅነቷ ከዓለም ሀገሮች መካከል የመጨረሻውን ዕርከን የያዘች መሆኗ ዘወትር ተደጋግሞ የሚገለፅ ስለሆነ ያንኑ መዘርዘር አስፈላጊ ሆኖ አናገኘውም ። ለዚህም ነው፥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ብሔራዊ ኢኮኖሚያችንን እንደምንም ብለን መገንባት ይኖርብናል የምንለው ። ለድኅነታችን ምክንያቶች የሆኑትን መሠረታዊ ችግሮቻችንን በሂደት ለመቅርፍ፥ ብሔራዊ ብልፅግናን ዒላማ ያደረገ የሕዝቡን ጥቅም ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ፥በገበያ ኢኮኖሚ መርኅ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል። ሰማንያ አምስት በመቶ የሀገራችን ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው በግብርና ላይ በመሆኑ፥ በዋናነት የመሬቱን ይዞታ መለወጥ ፥ መሬት ለአራሹ በባለቤትነት በህግ እንዲረጋገጥለት ማድረግ ወሳኝ ነው ። የሀገራችን አርሶ አደሮች በሚያርሱት መሬት የባለቤትነት ይዞታ በህግ የተረጋገጠላቸው ብቻ ሳይሆን፥ የመሸጥ የመለወጥ፥የማውረስ፥በዋስትና( በወለድ አገድ)የማስያዝ መብታቸው የማይደፈርና የማይገሰስ ሊሆን ይገባል ። መሬት አልባ የሆኑ አርሶ አደሮች፥ በኅብረተሰቡ ስምምነትና ድጋፍ የሚታረስ መሬት በንብረትነት ማግኘት የዜግነት መብታቸው ይሆናል። ዘመናዊ እርሻዎችን ለማቋቋም ለሚሹና ለሚችሉ በግብርና ለሚተዳደሩ ዜጎች መንግሥት የረዥም ጊዜ ውል ( በኮንሴሽን) ይሰጣል ።የሚሰጠውም መሬት፥መጠኑም ሆነ የይዞታው ውል ( የኮንሴሽኑ) ሁኔታ በህግ ይወሰናል ። መንግሥት ያርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲልና ምርቱም እንዲዳብር ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን ርዳትና አገልግሎት ለምሳሌ ምርጥ ዘሮች፥የሰብል ተባይ መከላከያ ፥ የግብርና መገልገያ መሳሪያዎችንና የመሳሰሉትን ከቀረጥ ነፃ የሚቀርቡበትን ሁኔታዎች ሊያመቻች ግዴታ አለበት ። አብዛኛው የሀገራችን ነዋሪ፥ ሕይወቱ የተመሠረተው በእርሻ ተግባር እንደመሆኑ ፥ ለገጠሩ ዜጋ ከኑሮው ጋር የተያያዙ አገልግሎት የሚሰጡ መጋቢ መንገዶች ፥ ትምህርት ቤቶች፥ክሊኒኮች፥ የዕደ ጥበብ ማሰልጠኛ ማዕከሎች ፥ የመስኖ ግድቦች ፥ ቦዮች ፥ የጉድጓድ ውሐ በአቅራቢያ የሚያገኝበትን ዘዴ ሁሉ ማመቻቸት የመንግሥት የሥራ ድርሻ ሊሆን ይገባል። ዘመናዊ የርሻ ዘዴን ለማስተዋወቅ፥የእንስሳትን ርባታ፥ የአትክልትና አዝርዕት፥ ዘፎችንና ደኖች ፥

የቤት እንስሳትን ርባታም÷ ሆነ የዱር አራዊትን ጠበቃና ደህንነት ለማረጋገጥ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ከጠቅላላው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተለይቶ የሚታይ አይደለም ። ወንዞችና ጅረቶች ለእርሻና ኢንዱስትሪ ጣምራ ግልጋሎት የሚሰጡበትን ዕቅድ ማውጣት የቅድሚያ ግዴታው÷የሀገሪቱ መንግሥት መሆኑ ቢታወቅም÷በዚህ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ÷ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱበትን ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል ። የሀገራችን አዕዋፍ ብሔራዊ ሀብታችን ስለሆኑ ÷ተንከባካቢ በማጣት ለዘመናት በመሰደድ ዘራቸው በመጥፋት ላይ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊው መከላከል ሊደረግላቸው ይገባል ። በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሀገር የሚሰደዱት ታላላቅ ወንዞቻችን በዘመናት እየጠራረጉ የሚወስዱት ለም መሬት ÷ ሀገራችንን ወደ ምድረበዳ እየለወጣት መሄዱን ያልተገነዘበና መፍትሄ ለማግኘት የሚቻልበትን መንገድ የማይሻ መንግሥትና ማነኛው ዜጋ ÷ ስለሀገሩ ኢኮኖሚ ዕድገት ይቆረቆራል ብሎ ለማሰብ ይቸግራል ። ታላላቅ ወንዞቻችን የኤሌክትሪክ መብራት ማመንጫ ኃይል መሆናቸው ቀርቶ ÷ ለም አፈራችንን እየዘረፉ ለባዕዳን መጠቀሚያ እንዲያደርጉ መፍቀድ የዛሬውን ነዋሪ ብቻ ሳይሆን ÷ የመጭውን ትውልድ ሀብት ማዘረፍ ይሆናል።

በዕርሻ ላይ የተመሠረተ እንዱስትሪ ( አግሮ- እንዱስትሪ ) ማስፋፋት ተመጣጣኝ የሆነ የዕድገት ርምጃ ማምጣት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎቱና ምኞቱ መሆኑ የታወቀ ነው ። ያልተነካው የሀገራችን ድልብ የተፈጥሮ ሀብት ÷ የከርሰ-ምድር ማዕድናትና ሌሎችም ቁልፍ ብሔራዊ ሀብት በሙሉ ለሕዝብ ጥቅም የሚሆኑበትን ሁሉ ማድረግ ከድኅንት እንድንላቀቅ ዋስትና ይሆናሉ ። ነፃ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ ÷ የባንክ የፋይናንስና የመድኅን ( ኢንሹራንስ) መስፋፋት በሀራችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሕግና ሥርዓት እንዲከናወን ማድረግ ÷ ማንም ድርጅት ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ያላግባብ እንዳይጠቀምበት ማገድ ወሳኝ ነው ። በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ፖለሲ የሕዝቡን ሙሉ ተሳትፎ የሚያስተናግድ እስከሆነ ድረስ ÷ከድኅነታችን ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረት ተገቢውን ሚና እንደሚጫወት እንረዳለን ። ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ግን ለጭፍን ብዝበዛ አሳልፎ የሚስጥ ጨካኝ ሰው በላ ሥርዓት እንዳይሰፍን ኢአሕፓ አጥብቆ ይከላከላል ። የሠለጠነውን የሰው ኃይል ጉልበት ከገበሬውና ከሠራተኛው ጋር እንዲሁም ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ጋር አስተባብሮ የዕድገት ጎዳና ለመቀየስ ÷በህግ የተመሠረተ ነፃ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መዘርጋት የግድ ነው ። ይህ ፖሊሲ ሀገራችንን የዓለም ተመፅዋች እንዳትሆን ከማድረጉም በላይ በራሳችን እንድንተማመን ያደርገናል ። በተሻለ መጠን ተመሳሳይ የዕደገት ዕርምጃ የሚያስገኝልንን የብሄራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መዘርጋት÷ ከድህነታችን ለመላቀቅ የሚረዳን መሆኑ ብቻ ሳይሆን ÷ ለአንድነታችን ጥንካሬም በእጅጉ ይጠቅማል ።

በዓለም ውስጥ እጅግ ድሃ ተብለው ከተፈረጁት 12 ሀገሮች መካከል ኢትየጵያ ሀገራችን አንዷ መሆኗን መረዳታችን ዘወትር የሚያሳዝነንና የሚያስቆጨን ጉዳይ ነው:: ከሃያ አምስት ዓመት በፊት ከተከሰተው ከዚያ አሰቃቂ ረሀብ በኋላ ፥ ዛሬ እንደገና ከአስራ ሦስት ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ለሌላ ረሀብ በመዳረጉ፥ የዓለም አቀፍን አስቸኳይ ርዳታ ለማግኘት እጁን ዘርግቷል :: የሕዝቡ ቁጥር በፍጥነት እያደገ መሄድና የምግብ አቅርቦቱ እጅግ ተመጣጣይ ባለመሆኑ ለርሀብተኛነትን የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል :: ከመቶ ሰባ አምስት የሆነው የገጠር ነዋሪ ሕዝብ ንፁህ የመጠጥ ውሐ አያገኝም :: ስድስት በመቶ የሚሆኑት የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች፥ የመጠጥ ውሐ ቀድቶ በእንስራ ተሸክሞ ለመምጣት በቀን ከስድስት እስከ ዘጠኝ ኬሎ ሜትር መንገድ በእግር ለመሄድ ይገደዳሉ :: የጤና ጉዳይ ከተነሳም ደግሞ ያለው ሁኔታ አሰቃቂ ነው ::አምራቹ ሀይል በወባና በዘመናዊ በሽታ መያዙ ዕድገት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው :: የበርካታ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች ባላቤት የሆነች ሀገራችን እስከዛሬ ድረስ ለዕርሻ መሬቷ የምትጠቀምበት የመስኖ ውሐ ከመቶ አንድ ነጥብ ስድስቱን ብቻ ነው:: ድህነት ብሔራዊ መለያዋ የሆነችው ሀገር፥በየዓመቱ ከአስራ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ርዳታ ማግኘቷ ቢመዘገብም፥ገንዘቡ ወደ ወያኔ ኪስ ስለሚገባ ድህነቷ ሊቀረፍላት አልቻለም :: ከዛሬ አስር ዓመት በፊት በቤኒን ዋና ከተማ ኮቶኑ የተደረገው ስምምነት ፥ የአውሮፓ ኮሚሽን ለኢትዮጵያ የሚያደርገው ርዳታ ከሰብዓዊ መብት መከበር ጋር መያያዝ አለበት የሚል ውሳኔ ማስተላለፉ ቢታወቅም ፥ ዛሬ የሀገሪቱ ዜጎች በግፍ እየታሰሩ እየተገደሉና በብዛትም በመሰደድ ላይ ናቸው :: በኢትዮጵያ ስም የሚጎርፈውም የውጭ ርዳታ የወያኔ ባለሥልጣናትና ወገኖቻቸውን ማበልፀጊያ ሆኖ ቀርቷል::አግላይ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓትና አድላዊ የሆነ የኦኮኖሚ ፓሊሲ፥የሀገሪቱን የጋራ ሀብት እየነጠቀ ለሥርዓቱ አቀንቃኞች መንደላቀቂያና መክበሪያ አድርጎታል::

ፀረ ኢትየጵያ አቋማቸውና የሕዝብ ጥላቻቸው የቱን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን ለመግለፅ ይሆናል፥ ወያኔዎቹ፥የሀገሪቱን የድንበር ግዛቶችና ለም የርሻ መሬቶች ለባዕዳን በመቸብቸብ ላይ የሚገኙት :: የኢትዮጵያ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 1 127 200 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን፥ ዛሬ 64 000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር (ከመቶ 6) የሚሆነው መሬት ለሱዳን ተሰጥቷል:: ይህ ለሱዳን የተሰጠው መሬት ከ 200 ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ ለመሆኑ ፥በዓለም አቀፍ ደረጃ የተረጋገጠ ነው:: ይህ በጠረፍ አካባቢ የተወሰደው የኢትዮጵያ መሬት ፥ ርዝመቱ 1600 ስኩዌሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን፥ ስፋቱ ደግሞ 40 ስኩዌሬ ኪሎ ሜ/ር ነው :: የጅቡቲን የመሬት ስፋት በሦስት ዕጥፍ ይበልጣል :: ይህ ወያኔ ለሱዳን የሸለገው መሬት በስፋቱና በለምነቱ ብቻ ሳይሆን፥

በውስጡ በሚኖሩ አራዊትና  እንስሳት ፥ አዝርዕትና ዕፅዋት ጭምር ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነው ።

በእኛ ዕምንት ፥ ማነኛውም  የፖለቲካ ሥርዓትም ይሁን የኢኮኖሚ ፖሊሲ  የአንድን ሀገር የልማት ርምጃ ሊያፋጥን  የሚችለው ፥ በቅድሚያ በሀገሪቱ  ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አውን ሲሆንና ቀጥሎም የኤኮኖሚው መሰረትና ይዘት ፥ የሀገርን ብሄራዊ ጥቅም ያስቀደመ ሆኖ ሲገኝ ነው ።የሕዝብን መሠረታዊ ነፃነትና መብት ማስከበርና የኢኮኖሚ ዕድገት ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም ። አንዱ ከሌላው  ጋር  ተደጋጋፊ  እንጅ   ተፃራሪ  አይሆንም ። በነፃ የመንቀሳቀስ መብት ከሌለ÷ በራስ  አነሳሽነትንና  አፍላቂነትን  መሠረት  ያደረገ  የልማት እንቅስቃሴ ማድረግ  ከቶ የሚቻል አይሆንም። በዘር ላይ የተመሰረተ የክልል አገዛዝ አዋቅሮ በጋራ ሀብት ላይ የተመሠረተ የጋራ   ዕድገትና  ብልፅገና  ሊመጣ  አይችልም  ። ከሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍላተ  ሀገር በሚዘረፍ ሀብት የአንድን አካባቢ ለማበልፀግ የተዘረጋ የልማት ዕቅድ ፥ዕድገትን ቀርቶ ሠላምንና መረጋጋትን አያስገኝም ። የእኛ የኢኮኖሚ ፖሊሲ  ራዕዩ ሰፊና በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኑሮ ዕድገት  ላይ ያተኮረ  ነው  ።  የሀገሪቱ  ብሔራዊ  ሀብት የጠቅላላው የሀገሪቱ ዜጎች የጋራ ሐብት መሆኑን ስለምናምን÷ ጠቀሚነቱና አገልግሎቱ ያለ ምንም አድሎ የሁሉም ዜጋ ነው ። **የዚህ ረዥም ራዕይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ  ዋስትናው÷ የህግ የበላይነት ÷የሰብዓዊ መብቶች ያለምንም ገደብ መስፈን÷ የሀገር ነፃነትና ሉዓላዊነት መከበር ነው።**

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ የባዕዳን ርካሽ ሸቀጥ ማራገፊያ በመሆኗ÷ መለስተኛ አቅም ያላቸው ነጋዴዎች ተጠቅተዋል። ብሄራዊ ኤኮኖሚን  የሚገነቡ  ነጋዴዎች  እንቅስቃሴና ዕድል ተዳክሟል ። አርሶ አደሩ   የመሬቱና  የላቡ   ተጠቃሚ  እንዳይሆን÷  በስግብግቦቹ የወያኔ  ቡድኖች ታግዷል ። ባዕዳን÷ በሀገራችን የውስጥና የውጭ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ያሻቸውን ለማድረግ ኃይልና ነፃነት አግኝተዋል። ይህም ሀገሪቱን  የእጅ  አዙር ቅኝ ግዛት አድርጓታል ለማለት ያስችላል  ።   የሀገራችንን    የፖለቲካ ችግር ፥  የኢኮኖሚ  ድቀት÷ የማኅበራዊ  ቀውስ÷ የሕዝቡንም ሁለንተናዊ መከራና ሮሮ ለማስወገድ በግድ ይህ ዘረኛ ሥርዓት መወገድ አለበት።

ፓኖራማ ቁጥር 86

መጋቢት 8 ቀን 2002

# የትዝብት አድማስ

## <u>የኢሕአፓ የትምህርት ፖሊሲ</u>

የሀገራችን ብሄራዊ የትምህርት ፕሮግራም ከሀገሪቱና ከሕዝቧ ታሪክ ፥ ባህልና ልምድ እንዲሁም ፍላጎት ጋር ተቀናጅቶ መራመድ አለብት ብሎ ኢሕአፓ ያምናል።

ትምህርት ከምርት ሥራ ጋር እንዳይነጠል ማድረግና መሃይምነትን ማጥፋት ፥ ድህነታችንን ለመዋጋት ፍቱን መድህኒት እንደሆነ እንረዳለን ።ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ህፃናት፥ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በህግ ተደንግጎ በተግባር ሊተረጎም ይገባል ። ሥርዓተ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍት በሙያው የሰለጠኑ ምሁራን ያዘጋጁት ሆኖ ፥ ወላጆችና መምህራን ተወያይተውበት የሀገሪቱ ምክር ቤት ከአፀደቀው በኋላ የሀገሪቱ ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ ሆኖ በተግባር ይተረጎማል ። የነፃ ትምህርት እንዲስፋፋ መጣር አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም ። የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ ሁሉን አቀፍ ለማድርግ ከተፈለገ ፥ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶችን ፥ የማታና የክረምት ትምህርት ቤቶችን የእንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎችን መመስረት የሀገሪቱ ዓይነተኛ የትምህርት ፖሊሲ መሆን አለበት ። የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ለቀዩ ክፍሎችና እንዲሁም ብቃትና ፍላጎት እያላቸው በችግር ምክንያት ትምህረት ለሚያቋርጡ ዜጎች የሚያስፈልጋቸውን ትብብር ማድረግ ተገቢ ነው ።ለተንቀሳቃሽ ከብት አርቢዎችና ልጆቻቸው ለአካባቢያቸው ተስማሚ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም ወይም መርሀ ግብር ሊዘጋጅላቸው ይገባል ። የመምህራኑን ሙያ የሚያዳብር ሥልጠና ፥ የደመዎዝ ሁኔታ እንደ ሁኔታው የሚሻሻልበትን እርምጃ መውሰድ ከትምህርት ፖሊሲው አንደኛው ክፍል መሆን አለበት ። የመምህራን በነፃ የመደራጀት መብት የተጠበቀና የተከበረ መሆንም አለበት ።

የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ፥ የልዩ ልዩ ሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች ፥ የጥናትና የምርምር ተቋማትን ፥ የከብት ርባታና የግብርና ማስፋፊያና ማሳደጊያ ማዕከልን ማብዛት እንደ

የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ አካል ተወስዶ በትጋት ሊሰራበት ይገባል ፡፡ ለኪነ ጥበብ ሰዎች ፥ ደራሲያን፥ ተዋናያን፥ መዘምራን፥ የዕድ ጥበብ፥ ፈጠራም ይሁን ግኝቶችን ለማምጣት የሚጥሩትን ዜጎች ሁሉ የተለየ ርዳታና እንክብካቤ ማድረግ ሀገራችንን ከኋላ ቀርነት አውጥቶ ወደ ሥልጣኔ ጎዳና እንደሚወስዳት የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡ ስለሆነም የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለየ አትኩሮት ሊያደርግ ይጠበቅበታል ፡፡ መንግሥት ለሀገሪቱ ህፃናት የተለየ እንክብካቤ በማድረግ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ ለዕድገታቸው የሚስማማ አካባቢ የሚያገኙበትን ዕድል ሊያዘጋጅለቸው ይገባል ፡፡ በጤናማ አካል ላይ የተገነባ አዕምሮ፥ ጤናማና ተመራማሪ እንደሚሆን የታወቀ ነው ፡፡ ስለሆነም፥ መንግሥት፥ የሀገሪቱ ህፃናትና ወጣቶች በአካል እየጠነከሩ ፥ በአዕምሮ እየጎለመሱ ማደግ እዳለበቸው ተገንዝቦ የተቻለውን ሁሉ ጥረትና እንክብካቤ ማድረግ ግዴታው ነው ፡፡ ስፖርትና ሙዜቃ የሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ አካል መሆኑን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ችሎታ ያላቸው ወላጆች፥ ልጆቻቸውን በግል ትምህርት ቤት ማስተማር መብታቸው መሆኑ ባይዘነጋም ፥ የመማሪያ መጽሐፍቱም ይሁን ሥርዓተ ትምህርቱ ፥ የሀገሪቱን ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ መከተል ይኖርበታል ፡፡ መቸውንም ቢሆን ፥ ለሀገራችን ታሪክ ፥ ባኅልና ለሕዝባችንም ልማድና ዕምነት ቀናዒ በመሆናችን ፥ በሥልጣኔና በትምህርት ሽፋን የሚመጡ አልባሌ የውጭ ባኅሎች የኢትዮጵያን ህፃናት አዕምሮ እንዳይበርዙ አጥብቀን እንከላከላለን ፡፡ በመሆኑም ፥ የሀገራችን ታሪክ በጎ ባህልና የሕዝቡንም ጠቃሚ ልማድ መጠበቅና ማስፋፋትን ኢሕአፓ የትምህርት ፖሊሲው መሠረት አድርጎ ይይዘዋል፡፡

ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን ጋር ተለይቶ የማይታየውና አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋግፎ የሚሄደው፥ብሄራዊ የትምህርት ፖሊሲያችን ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ለሀገር ዕድገትና ልማት መሠረታዊ ሚና ስለሚጫወት ነው ፡፡ የሠለጠነውን የሰው ጉልበት ፥ የገበሬውና የሠራተኛው ኀይል እንዲሁም ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ጋር አስተባብሮ የዕድገት ጎዳና ለመቀየስ በሁሉም ዘርፍ ትምህርትን ማስፋፋትና ከምርት ሥራ ጋር ማያያዝ በቅድሚያ ከርሀብ አለንጋ ለመውጣት በምናደርገው ጥረት በእጅጉ ይረዳናል ፡፡ ዘለዓለም በድኅነት አረንቋ መግባታች ባቻ ሳይሆን፥ ከዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ ለመቅረታችን ዋና ምክንያቶች ከሆኑት ውስጥ ፥ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ፥ የዕደ ጥበብና የቴክኒክ ተግባራት በሀገራችን አለመስፋፋት ነው፡፡ ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ፥ ጥናትና ምርምር ፥ ፈጠራና ግኝት በሀገራችን የትምሕርት ፖለሲ ውስጥ ሁነኛ ቦታ ተስጥቷቸው ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ እንመኛለን ፡፡ ይህን ምኞት ወደተግባር ለመተርጎም ፥ በግድ በሥርዓተ ትምርቱ ውስጥ የማትማቲክስ ወይም በደፈናው ሂሳብና የሳይንስ ትምህርት የተለየ አትኩሮት እንዲሰጠው ማድረግ የትምህርት ፖሊሲያችን ዓይነተኛ ዓላማ ነው ፡፡ የተማረ ሕዝብ ለሀገራችን ልማትና ዕድገት መሠረት ለመሆኑ ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስረዳት አንከጅልም ፥

*ምክንያቱም ዕድሉ ተነፍጎት ነው እንጅ፥ የትምህርትን ጠቃሚነት ለራሱ ሳይተርፈው ልጆቹን በላቡ ዋጋ እየከፈለ ከሚያስተምር ሕዝብ የበለጠ የሚያውቀው ስለማይኖር ነው ፡፡ ትምህርትና ጤና የተያያዘ በመሆኑ ፥ በልዩ ልዩ በሽታ ተጠቂዎች የመሆናችን አንዱ ምክንያት የትምህርት አለመስፋፋት መሆኑ ይሰማናል ፡፡ከዚህም በመነሳት ለሀገራችን ያለን የጤና ፖሊሲ በሁለንተናዊ መልኩ ተዛማጅነት አለው፡፡ መቸም የሀገራችንን ሁለንተናዊ ስር የሰደዱ ችግሮችን ዘርዝሮ ለመጨረስ ቢያስቸግርም፥ ለተለያዩ በሽታዎች ሰለባ የሆነው ሕዝብ ያለበትን ስር የሰደደ የጤና ችግር ግን እንዲሁ በአርምሞ የሚታለፍ እንዳልሆነ እንገነዘባለን ፡፡ ስር የሰደዱትን በሽታዎችንና ተውሳኮችን ለመዘርዘር በሙያው የሰለጠኑ ሀኪሞችና ባለሙያዎች የተግባር ድርሻ በመሆኑ ፥ያንን ለማድረግ አንሞክርም ፡፡ በቀላሉ ሊወገዱ ከሚችሉት አፍለኛ ተውሳኮች ጀምሮ ፥ ስር የሰደዱትንና የገነገኑ በሽታዎች ምክንያት የሚሰቃየውን ሕዝብ ከህመም ለማላቀቅ ፥ ሀገራዊ ፖሊሲ አውጥቶ በየፈርጁ ተግባራዊ ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ለዚህም መሠረቱ የሕዝብ ጤና ጥበቃና የተላላፊ በሽታዎች መከላካያ ፖሊሲ ነድፎ በሥራ ማዋል ነው ፡፡ ቢያንስ በሌላው የዓለም ክፍል በብዛት የተወገዱት ተውሳኮች፥ እንደ ኩፍኝ፥ ፈንጣጣ፥ ወባ፥ እንቅርት፥ ሜኒንጃይትስ ( ማጅራት ገትር) ፥ የመሳሰሉትን ሁሉ ለማስወገድ መጣጣር ይኖርብናል ፡፡ በወሊድ ምክንያት የሚያልቁትን የገጠሪቱን ኢትዮጵያ እናቶቻችን አሰቃቂ ሁኔታ በቦታው ሆነን ያየነው ስለሆነ ፥ የጎሌና ስቆቃ ከሚሰጡን የሀገራችን ችግሮች መካከል የመጀመሪያውን ቦታ ይዞታል ፡፡ በኢሕአፓ ዕምነት፥ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም እስከፈቀደ ድረስ፥ የጤና አገልግሎት ተቋማትን በገጠርና በከተማ በሚገባ ማስፋፋት በሽታዎችን ለመቆጣጠርና በሂደትም ለማስወገድ ያስችላል፡፡ጤናው ያልተጠበቀ ዜጋ ከድህነትና ከችግር ሊላቀቅ አይችልም ፡፡ የሀገራችንም ብሔራዊ ሀብቷ የዜጎቿ ጤንነትና ድህንነት ስለሆኑ፥ የዜጎቹን ጤና የመጠበቅ የመንግሥት ተቀዳሚ ኃላፊነትና ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡*

*የትምህርትና የጤና ፖሊሲያችን ዒላማ ያደረጉት፥የሀገሪቱ ዜጎች በረሀብ፥በጥማት፥እርዛት በወረርሽኝ የዘመኑ ቀሳፊ በሽታ ( በኤይድስ) በወባ ፥እንዲሁም በመጠለያ እጦት ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት በመከላለከልና በማስወገድ ፥ በነፃነት የመኖር ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ ነው ፡፡ የተማረ ሕዝብ ራሱን ከአምባገነኖች ጭቆና ቀንበር ነፃ ከማውጣቱም በቀር ሀገሩም በነፃነት እንድትኖር ይፈልጋል ፡፡ ራሱን ነፃ ያወጣ ሕዝብ ሀገሩን ከውጭ ወራሪ ኀይል ብቻ ሳይሆን ፥ ሰብዕናውን አስከብሮ ፥ ክብሩንና ታሪኩን ጠብቆ ከረሀብና ከችግር ተላቅቆ በዕድገትና ልማት ጎዳና እየተጓዘ ፥ ሀገሩን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተገቢዉን ቦታ እንድትይዝ ያደርጋል ፡፡ በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሠረተ የሀገሪቱ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት የተጠበቀ ሆኖ ዕድገትና ብልፅግና እንዲሰፍን፥ የተማረ ዜጋ መብዛቱ ወሳኝ ነው፡፡ ከዚሁ አንፃር የወያኔ አገዛዝ የሀገሪቷን የጤና ተቋም አፈራረሶና አዛብቶ*

እንዳለ የሚታይ ነው፡፡ የወያኔ የትምህርት ፖሊሲም ዘረኝነትን መሠረት ያደረገና በዚሁም መሠረት ብዙሁኑን ሊያደነቁር የተቃኘ መሆኑንም እናያለን፡፡ ይህን ሁሉ መቀየርና መብትን ከአንድነት አዛምዶ ዕውቀትን በማስፋፋት ላይ ያተኮረ፣ ብዙሀኑን የሚያስቀደም የትምህርት ፖሊሲ መስፈኑ በጣም አስፈላጊ ነው ብሎ ኢሕአፓ ያምናል፡፡ ለዚህም እየታገለ ነው፡፡

ፓኖራማ ቁጥር 88

መጋቢት ቀን 21 2002 ዓም

የትዝብት አድማስ

<u>የኢሕአፓ ፌዴራላዊ/ የፌዴራሊዝም ፖሊሲ</u>

ምን ጊዜም ቢሆን የዓላማችን መቅድምና መሠረት አድርግን የምንታገልለት፥ ዘመን የማይሽረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅም ማስከበር ነው። እርሱም፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭ በህግ የሚረጋገጥበትና በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሠረተ የሕዝብና የሀገር አንድነት የሚረጋገጥበት የዕምነት ፥ የሀሳብና የኀሌና ነፃነት የሚከበርበት ፥ በሕዝብ ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋም <u>ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት መመስረት</u> ነው ። የእኛ የፌዴራል ሥርዓት፥ ከወያኔው የዘረኛ ክልላዊ ከፋፋይ አገዛዝ፥ በዓላማም ይሁን በይዘት ፥ በራዕይም ይሁን ከዘላቂው የሀገራችን ጥቅም አኳያ እጅግ የተለየ ይሆናል ። የሀገሪቱን ዜጎች በብሔር ብሔረ ሰቦች ከፋፍሎ በጠባቡ ክልል ኮድኩዶ የሚያስቀር ከፋፋይ ሥርዓትን አስወግዶ ፥ ማንኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየትኛው የሀገሪቱ ክፍል ሳይሸማቀቅ እንደልቡ የሚኖርበት ፌዴራላዊ ሥርዓት መመስረት ማለታችን ነው ። እኛ ፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ብለን የምንመኛት ሀገር ፥ የህግ አውጭው ፥ የህግ አስፈጻሚውና የዳኝነት ሰጭው መንግሥታዊ ዘርፎች፥ ሥልጣናቸው ፥ ተግባራቸውና ኃላፊነታቸው በግልጽ ተለይቶ በተዋቀረበት ሥርዓት የተገነባ የፌዴራል ሥርዓት የምትተዳደር ሀገር ማለታችን ነው ። ይህ ፌዴራላዊ ሥርዓት በህግ ተረጋግጦ በተግባር ሊተረጎም የሚያስችል የህግ የበላይነት ሲሰፍን ብቻ ነው ብለንም እናምናለን ። ይህን ስንል ምን ማላታችን ነው ? በሕዝብ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋመው ምክር ቤት ( ህግ አውጭው ዘርፍ) ባለ ሁለት ክፍሎች ዘርፍ

( ባይ ካሜራል) እንዲሆን እንመኛለን ማለታችን ነው፡፡ አንደኛው ክፍል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስተዳደር አካባቢዎች የሕዝብ ብዛት ላይ የሚመሰረት ሲሆን ፥ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ፥ በፌዴራል የሕዝብ ስብጥር ላይ ተመስርቶ ሁሉም ብሄረሰቦች በእኩልነት የሚወከሉበት ነው ፡፡ የሁለቱም ክፍሎች አባላት በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ ማለታችን ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ መጀመሪያውና መጨረሻው የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በዝርዝርና በግልጽ እንዲሰፍሩ ማረጋገጥ ወሳኝ ነው ፡፡ የእኛ ፌዴራላዊ ሥርዓት የሚያተኩረው በብሔረሰቦች እኩልነት፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ልማት ላይ ነው ፡፡ ጂኦግራፊያዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን መሠረት ባደረገ ፌዴራላዊ አሀዶች ግንኙነት ላይ የተዋቀረ የአካባቢ አስተዳደር ( ራስ ገዝ) መብትን የሚያረጋግጥ ፌዴራላዊ ሥርዓት ለሀገራችን ይበጃል ብለን እናምናለን ፡፡ ይህንን ዕምነታችንን ሊያረጋግጥልን የሚችለው፥ የመድበለ- ፓርቲ ዴሞክራሲ ተሳትፎ የሚረጋገጥበት የፖለቲካ ሥርዓት ሲመሰረት ነው፡፡

ማዕከላዊው መንግሥት በፌዴራል አወቃቀር ሥርዓት ከሚተዳደሩ የክፍለተ-ሀገር የራስ ገዝ የተለየ የሚያደረገው በሦስት መሠረታዊ ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖረው ሥልጣንና ኃላፊነት ብቻ ይሆናል፡፡ ይኸውም በኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ፥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ገንዘብና በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት የሀገሪቱ ዐበይትና ጥቃቅን ጉዳዮች በሙሉ የየክፍለ ሀገራቱ ሥልጣን ፥ ኃላፊነትና ተግባር እንዲሆን በሀገሪቱ ብሔራዊ ምክር ቤት ተዘርዝሮና ተደንግጎ በተግባር እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ በእኛ ተስፋና ራዕይ ይህ ዓይነቱ ፌዴራላዊ አወቃቀር ሥርዓት፥ ሌሎች ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ፥ ቢያንስ የሀገራችንን ሦስት መሠረታዊ ችግሮች በሂደት እያቃለሉ ያስወግዳሉ ብለን እናምናለን፡፡ ለሕዝብ የቆመ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ሲመሰረትም በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ላይ ተመርኩዞ ግዴታውን ከተወጣ፥ ለነዚህ ችግሮች መፍትሄ የማያመጠበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህ የፌዴራል አወቃቀር፣ለአስተዳደር ቅልጥፍና ፥ለፈጣን የዳኝነት ተግባርና ለልማትና ዕድግት እንቅስቃሴ አመች ሁኔታን ይፈጥራል ፡፡ ዛሬ የሀገራችን ሕዝብ ከማንኛውም ጉዳይ በበለጠ የተቸገረባቸው ጉዳዮች ቢኖሩ፥ የአስተዳደር ጭቆና፥ የዳኝነት ፍትሃዊ ተግባር መጥፋትና የልማት እንቅስቃሴ አድላዊነት ናቸው ፡፡ እነኝህ የሀገሪቱ መሠረታዊ ችግሮች ለአንድየና ለመጨረሻው መፍተሄ ካላገኙ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከችግር ወጥቶ፥ ፍትኀ-ርትዕ አግኝቶ ከመከራና ከስቃይ ነፃ ይወጣል ተብሎ አይታሰብም ፡፡

በወያኔ ዘረኛ የአፓርታይድ መሰል ጭቆና ስር ያላቸው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከተቆረሰችና የምዕራቡም ግዛቷ ለባዕድ ከተሸጠ በኋላ አሁን ያላት ቀሪው መሬት ስፋት አንድ ነጥብ አስራ ሦስት ሚሊዮን እስኩዌር ሚትር ወይም 437 794 እስኩዌር ማይል ሲሆን ፥ በዚህ የመሬት ስፋት ላይ የሚኖሩ ዜጎቿ ቁጥር ሰማኒያ አምስት ነጥብ ሁለት

ሚሊዮን ( 85.2 ሚሊዮን) እንደሆነ የዓለም አቀፍ የሕዝብ ቆጠራ ሰነድ መዝግቦታል ። በመካከለኛ ስሌት ሲገመት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በህይወት የመቆየት ዕድሜው አምሳ ሁለት ዓመት ብቻ እንደሚሆንም ተመዘግቧል። የሀገሪቱ ዜጎች የነፍስ -ወከፍ የዓመት ገቢ ሁለት መቶ ሰማንያ ( $ 280.00) የአሜሪካ ዶላር እንደሆነ በቅርቡ የወጣው ዓለም አቀፍ መረጃ ያመልክታል ። ይህም ኢትዮጵያን በዓለም ካሉት ደሃ አገሮች ውስጥ በመጨረሻው ዕርከን አስቀምጧታል።ይህም ማለት ታዲያ ዛሬ በዓለም ውስጥ ከተመዘገቡት ሁለት መቶ አስር (210) ሀገሮች መካከል ፥ የኢትዮጵያ ደረጃ ሁለት መቶ አምስተኛ (205) እንዲሆን አድርጎታል ማለት ነው። በዚህ የዓለም ሀገሮች ሰንጠረዥ ምደባ ፥ ከኢትዮጵያ በታች የተመደቡት ሀገሮች አራት ብቻ ናቸው ። ይህ ደግሞ ለኛ ኢትዮጵያውያን “ አራት ሀገሮችን በሀብት በልጠናል ! ተመስገን ! ”ብለን የምንዝናናበት ሊሆን አይችልም ። ጠንክርን ሁኔታውን በመለወጥ ከድህነት የምንወጣበትን ሁኔታ ለማመጣት ግን አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ እንዳለብን ያስገድደናል ። ይህ ውነታ ሊያስረዳን የሚችለው ነገር ቢኖር፥ የሀገራችንን ዕውነተኛውን ገፅታ ነው።ይህች ታላቅና ሰፊ ሀገር ፥ የነዋሪዎቹም ቁጥር እጅግ ብዙ የሆነ መሆኑን ተረድተን በግድ የፌዴራል ሥርዓት የሚያስፈልጋት መሆኑ አያከራክርም ።

የትግራይን መሬት የቆዳ ስፋት ከአጎራባች ክፍለተ-ሀገር መሬት ቀምቶ እያስፋፋ ፥ በተፃራሪው ደግሞ የሀገሪቱን ዳር ድንበር እያጠበበ ለባዕድ ሀገር በመሸንሸን ላይ ያለው የወያኔ ቡድን ፥ በዘርና በቋንቋ መለኪያ ላይ የተመሰረተ አወቃቀር በመዘርጋት የሀገሪቱን መላ ብሔራዊ ሀብት ለአንድ አካባቢ ልማት እያዋለና ለራሱም እየዘረፈ ፥ የፌዴራል ሥርዓት መስርቻለሁ ብሎ ለመቀለድ ይሞክራል ። ለም መሬቶችን ከወሎና ከጎንደር ክፍላተ-ሀገር ዘርፎ ወደ ትግራይ ክልሉ አስገብቶታል። ከሌሎች ወገኖቹ ጋር መከራውንና ደስታውን በመካፈል ለኢትዮጵያ ነፃነትና ክብር ሲል የተሰዋን የጎንደርንና የወሎን ሕዝብ አፀመ-ርስትና ሀብት በመዝረፍ ላይ የሚገኘው ይህ ዘረኛ የወያኔ ቡድን ፥ የሁለቱን ክፍላተ-ሀገር ዜጎች ክብርና ታሪክ በማዋረድ ላይ ቢገኝም፥ዛሬ እነዚህ ጥቃት የደረሰባቸው ዜጎች ቅድሚያ የሰጡት፥ በአሁኑ ወቅት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ኢትዮጵያን ከወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ለማላቀቅ በሚያደረገው ትግል ላይ ነው ። በመሆኑም የዛሬውን የግል ጥቃታቸውን በይደር ለማቆየት ተገድደዋል ። ነገ የሕዝብ አቸናፊነት ሲረጋገጥ ግን በግፍና በኃይል የተወሰደባቸውን መሬታቸውን፥ ቢቻል በህግ ካልሆነ ደግሞ በኃይል እንደሚያስመልሱ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። ይህ በደልና ጥቃት ነገ ፍትኅ ርትዕ አግኝቶ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ግን ፥ በየአንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ የተዳፈነ እሳት ሆኖ ይቆያል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬትን የሚያየው ፥ እርሶ ሰብል ለማምረትና የኢኮኖሚ ችግሩንም ለማቃለል የሚጠቀምበት የምርት ማምረቻ መሳሪያ/ ሀብት ብቻ ሳይሆን ፥ ከባህሉ ፥ ከታሪኩ ፥ ከትውልዱ ፥ ከዕምነቱና ከማንነቱ መግለጫ ጋር የተየያዘ በመሆኑም ጭምር ነው ። የወያኔ ቡድን ይህንን ሁሉ በግምት ሳያስገባ የጎንደርንና የወሎን መሬት በመዝረፉ፥ በነዋሪዎቹ ላይ ታሪክና ትውልድ የማይረሳው ብሄራዊ ወንጀል ፈጽሞባቸዋል።

የፌዴራል ሥርዓትን የምንመኘው፥ ለአስተዳደር ቅልጥፍና፥ ለተፋጠነ የፍርድ ብያኔን ለማግኘትና ለልማት እንቅስቃሴ እርምጃ ለማምጣት ብቻ ሳይሆን፥ የሀገሪቱ ብሔራዊ ሀብት የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት በመሆኑ፥ ሁሉም ዜጋ ያለ አድሎ በትክክል ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ለማረጋገጥም ጭምር ነው። ለዘመናት ተባብሮና ተከባብሮ በኀብረት የሀገሩን ዳር ድንበር በመጠበቅ አብሮ የኖረን ሕዝብ ፥ እንደ ድንጋይ ዘመን በዘር የከለለ የአፓርታይድ ሥርዓት ለሀገራችን አንድነት ለሕዝባችን እኩልነት ለዜጎቿም ብልፅግና ፥ ዕድገትና ሠላም አያመጣም ብለን ስለምናምን አጥብቀን እንቃወመዋለን ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን ታግሎ በመጣል በሚያመጠው የዴሞክራሲ ሥርዓት ፥ የራሱን ብሔራዊ ምክር ቤት ሲያቋቁም ፥ ምን ዓይነት ፌዴራላዊ ሥርዓት እንደሚመርጥ ስለምናወቅ ፥ በዘር ላይ የተመሰረተውን የወያኔን የጎሳ ፌዴሬሽን አሽቀንጥሮ እንደሚወረውረው ማንም ዜጋ አይጠራጠርም።

ፓኖራማ ቁ 87

የትዝብት አድማስ

የካቲት 27 ቀን 2002 ዓም

<u>የኢሕአፓ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ</u>

ኢትዮጵያ ሀገራችን በገለልተኝነትና በሠላም ፈላጊነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መከተል እንደሚኖርባት ኢሕአፓ ያምናል ። በዚህ መሠረታዊ መርኅ ላይ በመመርኮዝም ብሔራዊ ጥቅሟን በመጠበቅና በማስጠበቅ በነፃነትና በሰላም ከዓለም ሀገሮች ጋር አብሮ ለመኖር ምኞቷ ይሆናል።በመሆኑም፥በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀብ ከተጣለባቸው በስተቀር ከማንኛወም የዓለም ሀገሮችጋር በሰላም አብሮ በመኖር፥ በእኩልትና በጋራ ጥቅም መሠረት ግንኙነቷን ታካሂዳለች ፤ታጠናክራለች ። ይህ መሠረታዊ ፖሊሲዋም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የበለጠ በሰላምና በመተባበር አብሮ ለመኖር ያስችላታል ። ከዚህም በቀር ለፍትኅ ለዴሞክራሲ፥ ለነፃነትና ለስብዓዊ መብቶች ለሚታገሉ ሕዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያ ድጋፍ አይለያቸውም ። <u>ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፥ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም መጠበቅና የሌሎችንም ማክበር የውጭ ፖሊሲዋ የማዕዘን ዋልታ ሆኖ ይኖራል።</u> በራስ ነፃነትና ልዕልና ላይ ተመርኩዞ የሚተረጎም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማለት ለኢሕአፓ አዎንታዊ ገልልተኝነት ማለት ነው ። ይህም ማለት፥ ከማንኛውም የዓለም ነፃ ሀገሮች ጋር የሠላም ፥ የንግድ ፥ የባኅል ፤ የትምህርት ፥ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ግንኙነትና ትብብር እያደረገች ብሔራዊ ጥቅሟን ሁሉ ለማስከበር የተቻላትን ሁሉ ትፈጽማለች ማለት ነው። ከማንም ጎራ ጋር ወገን ሳትለይ በነፃነቷ ከሁሉም ጋር ወዳጅነት ለመመስረት በምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ገደብ ሊኖርበት አይችልም ።ይህም ለነጻነቷ ዋስትና መረጋገጫ ከመሆኑም በላይ ፥ ለውጭ ዲፕሎማሲዋ እንቅስቃሴ ተዓማኒንትን ያተርፍለታል። ይህ ፖሊሲ በአሁኑ ወቅት ሰፍኖ ያለውን የወያኔን ተንበርካኪ መሪዎች ባህርይና ድርጊት በጽኑ የሚጻረርና የሚቃወም ነው ። ኢትዮጵያ ሀገራችን የማንም ሀገር ጥቅም አስጠባቂና ፖሊሲ አስፈፃሚ ሀገር እንድትሆን ኢሕአፓ በጭራሽ አይፈልግም፤አይፈቅድም ።

የማንኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲ የዚያው ሀገር የውስጥ ፖለቲካና አስተዳደር ቀጥታ ነፀብራቅ እንደመሆኑ ፥ የሀገራችን የውጭ ፖሊሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ አክብሮትና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከተፈለገ፥ ሀገራችን የውስጥ አስተዳደሯና ፖለቲካዋ በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ መመስረት ይኖርበታል ። በመሆኑም ኢትዮጵያ ዜጎቿን በዴሞክራሲ ሥርዓት

እንዲተዳደሩ ከማድረግ ሌላ አማራጭ ሊኖራት ይችልም ። የኢሕአፓ የዲሞክራሲዊ ሥርዓት ራዕይ፥ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍሮ የሚቀርና ለይስሙላ ተብሎ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የሚሆን የቧልት ዴሞክራሲ ሳይሆን ፥ሕዝብ ያለተጽዕኖ በቀጥታ የሚሳተፍበት አሳታፊ ዴሞክራሲ ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዕለት ጉርሱ፥ለዓመት ልብሱና ለመጠለያው ከማሰብና ከመጨነቅ አልፎ ተርፎ፥ ስለ ጠቅላላ ኑሮውና ሕይወቱ፥ ስለ መሠረታዊ ጎልውናው ፥ስለሀገሩ ሁለንተናዊ ጉዳይ፥ ስለነፃነቱና ታሪኩ ፥ ዕምነቱና ባኅሉ ፥ስለ ወደፊቱ ዕድሉና ራዕዩ፥ስለ ፖለቲካ ፥ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ህይወቱ፥ስለ ሚመሰረተው መንግሥትና ስለሚመርጣቸው መሪዎች ፥በነፃ ተወያይቶና ተሳትፎ የሚወስንበት የፖለቲካ መልከዐ ምድር ሊመቻችለት ይገባል፡፡ የሕዝብ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰምረው ፥ የዜጎች ሙሉ ተሳትፎ ሲኖር እንደሆነ ግልፅ ነው ። በመሆኑም ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መርሆ እንድትከተል ማድረግ ፥ ሀገራችን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ኅብረተስብ አባል እንደትሆን ያስችላታል፡፡ እስከዛሬ ድረስ ሀገራችን ዘወትር የውጭ ተመጽዋች ሆና የቆየችው፥ የተፈጥሮ ድሃ ሆና ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ ዜጎቿ ሥራ የማይወዱና ታታሪ ባለመሆናቸው ሳይሆን፥አሳታፊ ዴሞክራሲ አግኝተው ኢኮኖሚያቸውን በመገንባት ከድኅነት ለመላቀቅ ባለመቻላቸው ነው ። ዛሬ የሀገሯን ኢኮኖሚና ባጀት በውጭ ርዳታ ላይ የመሠረተች ብቸኛ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ መሆኗ ዓለም የአወቀው ፀሀይ የሞቀው ሆኗል፡፡ በየትኛው የዓለም ታሪክ በውጭ ርዳታ ብቻ ከድኅነት ተላቅቆ ራሱን የቻለ ሀገር አይገኝም፡ የአንድ ሀገር ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው በመቆም ሀገራቸውን ከችግር ለማውጣት የሚችሉት ፥ ዜጎቹ በዴሞክራሲ ሥርዓት የራሳቸውን መንግሥት ሲመሰርቱና መሪዎቻቸውንም ሲመርጡ ብቻ ነው ።እስካሁን ድርስ የተለያየ ቀለምና ለምድ እያጠለቁ የተፈራረቁት የሀገራችን አምባገነን መሪዎች ፥ከአንድ ጽንፍ ወደ ሌላው ጽንፍ እየተወራጩ የየራሳቸውን የሥልጣን ዕድሜ በማራዘም፥ የጭቆና አገዛዛቸውን በሕዝቡ ላይ ከመጫን በቀር ለታሪክ የሚሆን መልካም ትዝታን አላስመዘገቡም ።ይህ በበኩሉ የሀገራችንን የውጭ ፖሊሲ ዘወትር የምዕራባውያን ተጠማኝና ደጀጠኝ አድርጎት ኖሯል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃዋ ኢትዮጵያ ነፃ የውጭ ፖሊሲዋን የምትመራበትን ቀን በናፍቆት የሚጠብቀውም በዚህ ምክንያት ነው ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ልክ እንደሌሎቹ በልማት ወደኋላ የቀሩ ሀገሮች ሁሉ የውጭ ርዳታና ትብብር እንደሚያስፈልጋት የሚያከራክር አይደለም ። በተለይ በሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ፥ ዕደ-ጥበብና መሃንዲስ፥ የቴክንክ ተግባራትና ትምህርት፥ ፋይናንስና የዕርሻ ዘዴ፥የመሳሰሉትን ዘመናዊ ርዳታ ማግኘት አለባት፡፡በገለልተኝነት ስም ብቻ በሯን ጠርቅማ ከዓለም ሥልጣኔ ተገልላ ልትኖር አትችልም ። ይህ ስለተባለ ግን ፤ በልማትና በርዳታ ሰበብ የሀገሪቱን ለም መሬት ለባዕድ አሳልፎ መስጠቱን ኢሕአፓ አጥብቆ ይቃወማል ። ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት፥የሀገሩን ለም መሬት ለባዕድ ሀገሮች መጠቀሚያ እንዲውል በሀራጅ ይሸጣል ተብሎ ይታሰባል ለማለት ባይቻልም ዛሬ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይኑ እያየ ጆሮው እየሰማ የመሃል አገሩ ለም መሬት ብቻ ሳይሆን፥ ጳር-ደንበሩም ጭምር ለባዕድና ለጉረቤት ሀገሮች እየተቸበቸበ ይገኛል። የሀገሩን ብሄራዊ ጥቅም በዚህ የከሃዲ ደረጃና ስፋት አሳልፎ የሚሰጥ ቡድን በሥልጣን ላይ ሲመጣ ማየት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመጀመሪያው ጊዜ መሆኑ ቢያሳዝነውም ተስፋ ሳይቆርጥ ሁኔታውን በመለወጥ ነግ - ተነገ ወዲያ የሀገሩን ጥቅም እንደሚያስከብር ግን ማንም ዜጋ ሊጠራጠር አይችልም። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩን ብሔራዊ ጥቅምም ይሁን የራሱን ነፃነት የሚጠብቅለት ኢትዮጵያዊ መንግሥት እንደሌለው አምኖ የራሱን መንግሥት ለማምጣት እየታገለ ይገኛል ። የራሱን መንግሥት መስርቶም ሀገራዊ ነፃነቱንና ብሔራዊ ጥቅሙን እርሱ ራሱ ማስከበር እንደሚችል ያለፈ ታሪኩ ስለሚመሰክርለት ፥ በዚህ በኩል ጠላቶቹ ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል ።

ለሀገራችን ኢትዮጵያ የምንመኝላት የተሟላ ነፃነትን ነው ስንል፥ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን ለማውለብለብና ፈንጠዝያን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን፥ በሁለንተናዊ ገጽታው ለሀገራችንና ለሕዝባችን በዘለቄታ መልኩ የሚጠቅም ነፃነት ማለታችን ነው። ይህ ምን ማለት ነው? የፖለቲካ ነፃነት ያለ ኢኮኖሚ ዕድገትና ጥንካሬ፥ያለ ዕርሻ ልማትና እንዱስትሪ መስፋፋት፥ ያለ ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ርምጃ በምንም ዓይነት ሀገራችን የተሟላ ነፃነት ይኖራታል ተብሎ አይታሰብም ማለት ነው ። ሀገራችን ከረሀብ ፥ ከበሽታ፥ ከመሀይምነት ፥ ከድኅነት፥ በጠቅላውላም ከኋላ ቀርነት እንድትላቀቅ ካስፈለገ፥ የእጆቿን የመዘርጋት አቅጣጫ መለወጥ አለባት። እጆቿን ለዕርዳታ ወደ ምዕራባውያን ከመዘርጋት ይልቅ፥ ወደ ሕዝቧ፤ ወደ መሬቷ፥ ወንዞቿና ወደ ከርሰ-ምድሯ ዘርግታ የራሷን አንጡራ ብሔራዊ ሀብቶች መጠቀም መቻል ይኖርባታል። ድልብ ሀብቷንና ወንዞቿን ለመጠቀም በምትሞክርበት ጊዜ የቅርብና የሩቅ ተቀናቃኞቿ እንቅፋት እንደሚሆኑባትም አስቀድመን ልንገነዘበው ይገባናል።የፖለቲካ ነፃነታችንን አስከብረን ወድ ልማት አቅጣጫ በምናተኩርበት ወቅት ሊገጥመን የሚችለውን ማነኛውንም ዕንቅፋት ለማቋቋም አስፈላጊውን ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንዳለብን፥ ብሔራዊ የሆነ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን ይገባል። በአሁኑ ወቅት ይህ ሊሆን አልቻለም። በእኛ ዕምነት ፥ሀገራችን ከአካባቢና ከሩቅ ጠላቶቿ ጥቃት ለመከላከልና የውስጥ ፀጥታዋንም አስከብራ ያለስጋት ወደ ልማቷ ለማተኮር ካስፈለጋት፥ሦስት ብሔራዊ ተቋማት ተጠናክረውና ተቀናጅተው በቅንብር እንዲሰሩ መደረግ አለባቸው ። እነርሱም የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፥ የመከላካያ ኃይልና የኢንተሊጀንስ ድርጅት ናቸው ። በዓላማ ፥በተልዕኮና በይዘት የተለያዩ ተቋማት ሊመስሉ ቢችሉም ፥ የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ጥቅምና ሀገራዊ ደህንነት በመጠበቅ በኩል አንድም ሦስትም መሆናቸው ታውቆ፥ በአስተማማኝ ደረጃ ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚሰሩባት መንገድ ሊኖር ይገባል።ሀገራችን የተጣራ ኢንተሊጅንስ በአስተማማኝ ደረጃ እንዲኖራት ማድረግ፥ እንደ መጀመሪያው

የመከላከያ መስመር ሊቆጠርላት ይችላል፡፡ “ ትንሽ ልሙትና ወዳጅ ጠላቴን አውቄ ልምጣ /ልነሳ፡፡ ” እንደሚባለው፥ በሞትና በሽረት መካከል የምትገኘው ሀገራችን ፥በዚህ አስተዛዛቢ ዘመን ፥ከልጆቿ በስተቀር የቅርብ ጎረቤትም ይሆን የሩቅ ዘመድ እንደሌላት አረጋግጣለች ፡፡ የአንድ ሀገር የውጭ ዲፕሎማሲ የሚመሠረተው፥ “ ቋሚ ወዳጅ ወይም ዘላቂ ጠላት የሚባል ነገር የለም፥ ሊኖር የሚችለው ግን ዘላቂ ጥቅም ብቻ ነው ፡፡ ” በሚል ይትበሃል ላይ መሆኑ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ እንዲያው ለመሆኑ፥ በዚህ ተለዋዋጭ ዓለም ቋሚ ወደጅ ይኖረኛል ብሎ ሊያስብ የሚችል የትኛው ሀገር ሊሆን ይችላል ? ሁለት የዓባይ ወንዝ ተጠቃሚ ሀገሮች፥ጥቅማቸውን በበለጠ ለማስጠበቅ የሚያስቸላቸውን ዕድል ለመግኘት ለብዙ ጊዜ ሲጠባበቁ ኖረው ይኸው ዛሬ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ ቡድን ስላጋጠማቸው ላሜ ወለደችልኝ ብለዋል ፡፡ ነገ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ቀናዒ ኢትዮጵያዊ ኃይል ሲመጣ ሁኔታው እንደሚለውጥ ማን በነገራቸው ? በዕርግጥም ሀገራቸውን ከጥቃት አድነው ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስጠብቁላት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ብቻ እንደሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ፡፡ ይህ ታውቆ በመጀመሪያ ደረጃ ፥ ማነኛውም ብሄራዊ ፖሊሲ ሊወጣና ሊቃኝ የሚገባው የሀገሪቱን ኅልውና ከአደጋ ለማዳን አንፃር መሆን አለበት ፡፡ ምንም ተባለ ምን፥የማነኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲ የሚነደፈው የዚያኑ ሀገር ብሄራዊ ደኅንነትና ዘላቂ ጥቅም ከመጠበቅ አኳያ በመሆኑ የኢሕአፓም የውጭ ፖሊሲ መመሪያ የሚቃኘው በዚህ መሠረታዊ መርኅ ላይ ነው፡፡

ፓኖራማ ቁጥር 84

የትዝብት አድማስ

ጥር 16 ቀን 2002 ዓም

## ኢሕአፓና የኢትዮጵያ የመከላከያ ፖሊሲ

የፓርቲው መሠረታዊ ዓላማ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይበጃል ብሎ ባመነባቸው ሀገራዊ ፖሊሲዎች ላይ ቅድሚያና አፅንዖት በመስጠት በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሕግ መንግሥት ውስጥ ቦታ እንዲሰጣቸው መታገል ነው ። በፖለቲካ ፕሮገራሙ ውስጥ አስገብቶ፥የሚሻሻሉትንም በሂደት እያስተካከለ የትግሉ ማዕከል እንዲሆኑ አድርጎ እስከዛሬ ድረስ በመታገል ላይ የሚገኘውም ለዚህ መሠረታዊ ዓላማ ብቻ ነው ። እነኝህ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ግን በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉት ፥ በሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት በአስተማማኝ ደረጃ ሲረጋገጥ ለመሆኑ አሌ የሚባል አይደለም ። በፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ሀገራዊ ፖሊሲዎችን ህያው ለማድርግ የሕዝቡን ሙሉ ነፃነት፥ ሀገራዊ ሉዓላዊነትና የህግንም የበላይነት መሠረት ያደረገ የኢትዮጵያ ሕግ መንግሥት ሲመሰረት ብቻ የሆናል ። ሕገ መንግሥትን ያህል መሠረታዊና ቋሚ ብሔራዊ ሰነድ ሕያውነቱን የሚያስመሰክረው ፥በአሳታፊ ዴሞክራሲ የዜጎችን ዕለታዊ ሕይወት በዕለት ተዕለት በተግባር ሲተረጎም ነው።

መሠረታዊ የሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ፖሊሲዎችን አስመልክቶ ለሕዝብ ማሳወቅ የፓርቲው ግዴታውና ተግባሩ በመሆኑ ፥ እስከዛሬ ድርስ ሲያደርገው እንደቆየው ሁሉ ፥ ዛሬም እንዳስፈላጊነቱ በተከታታይ እየዘረዘረ ያቀርባል ። በመሆኑም፥ ዛሬ የምናተኩረው በሀገሪቱ የመከላካያ ፖሊሲ ላይ ይሆናል ።በሕዝብ አዎንታ ላይ በተመሰረተ ሕገ መንግሥት ውስጥ የሚሰፍሩትን የሕዝቡን መብቶች የሚያከብር እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎቶችና ጥቅሞች የሚጠብቅ የሀገሪቱንም ድንበርና ሉዓላዊነት የሚከላከል የጦር ኃይል፥ የሕዝቡንም ሠላምና ፀጥታ እየጠበቀ ህግና ደንብ የሚያስከብር የፖሊስ ሠራዊት በህግ ማቋቋም፥ ለሀገራችን ነፃነት ዋስትና ነው ብለን እናምናለን ። ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያላገለለ፥ አስፈላጊ መስፈርቶችንም በሚያሟላ መልኩ ተመልምሎ የተውጣጣ፥ በሙያው የሰለጠነ፥ ታማኝነቱ ለሀገሩና ለሕዝቡ ፥ ታዛዥነቱ ደግሞ በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት የሆነ ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል መመስረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት እንደሆነ እናምናለን ። የጦር ኃይሉና

የፖሊስ ሠራዊት አባላት የሚቀጠሩት በፈቃዳቸው ሆኖ፥ የውዴታ-ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ግን ይገነዘቡታል ::የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት አባላት ሙያቸው በፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ለማግባት ባይፈቅድላቸውምና ደግሞም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድርግ የተከለከሉ ቢሆኑም ፥በሀገሪቱ የፖለቲካ ሕይውት ውስጥ ተሳትፏቸው ፥በመምረጥና በውሳኔ ሕዝብ ( ሬፈራንደም) በመሳተፍ ብቻ ይሆናል ::ይህም በመሆኑ ፥ የማነኛውም የፖለቲካ ድርጅት / ቡድን ወይም ስብስብ አባል ሊሆኑ አይችሉም :: በፖለቲካ ለመስተፍም ይሁን የድርጅት አባል ለመሆን የሚፈልጉ የመከላካያና የፖሊስ ኣባላት በቅድሚያ ከሠራዊቱ መሰናበት አለባቸው :: የመከላካያና የፖሊስ ሠራዊት ኣባላትን ደኅንነት መጠበቅ ፥ የጡረታ መብታቸውን ማስከበር ፥ በግዳጅ ላይ ለተሰው አባላት ቤተሰቦች ተገቢውን ዕርዳታና እንክብካቤ ማድረግ ከመከላካያ ፖሊሲያችን ውስጥ ሁነኛውን ቦታ ይይዛል :: ከዚህም በቀር ፥ በሀገራችን በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የጦር ሰፈሮች መቋቋም አጥብቆ የተከለከለ መሆኑና፥የጦርና የወታደራዊ ጥገኝነት እንዳይፈጠር ማድረግ የመከላከያ ፖሊሲያችን መሠረት ነው ::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላካያ ሠራዊት፥ የተመሠረተበትን ዓላማና ግዴታ ለመፈፀምም ሆነ፥ ተልኮውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችለውን ሥልጠና ፥ ትጥቅ ፥ አደረጃጀትና ስንቅ ለሚሟመላት የሚያስፈልጉት የትምህርት ተቋማት ሁሉ ተሟልተው ሊቋቋሙለት ይገባል:: ልዩ ልዩ የሙያ ዘርፎቹን ለሚሟላት ብቻ ሳይሆን፥መሠረታዊ የሆነውን ወታደራዊ ሳይንስን ለማስተማር የሚያስችሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ወታደራዊ አካዳሚዎች፥ የአየር፥ የየብስና የባህር መከላካያ ዘመናዊ መሳሪያዎች ሁሉ ተሞልተው መገኘታቸው አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑን የሀገሩ ነፃነት ዋስትና እንዲኖረው የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ሊገነዘበው ይገባል :: የሀገሪቱ ብሔራዊ ሀብትና የኢኮኖሚ አቅም በፈቀዱት መጠን፥ ሀገራችን ለራሷ መከላካያ የሚያስፈልጓትን የጦር መሳሪያዎችን ፥ የትጥቅና የስንቅ፥የመጓጓዣና የመገናኛ አገልግሎት፥የኤሌክትሮኒክስ ቴክኒዮሎጅ ዕቃዎቿን የምታመርትባቸው ፋብሪካዎችና ተቋሞች እንዲኖሯት ማድረግ ፥ የመከላከያ ሠራዊቷን ብቃትና ዝግጁነት ያረጋግጥላታል ብለን እንመኛለን :: ከአፍሪካ አህጉር በቆዳ ስፋቷ በሦስተኛ ደረጃ የተመደበችውና የሕዝቧም ቁጥር ከሰማኒያ ሚሊዮን በላይ የሆነች ሀገር፥ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ ከምትሰጣቸው ሀገራዊ ፖሊሲዎች መካከል፥ የመከላከያ ኃይሏን ማጠንከር ለመሆኑ የሀገሩን ህልውና መጠበቅ የሚመኝ ዜጋ ሁሉ ይስማማበታል::

ከሰሃራ በረሀ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ በትጥቅም ሆነ በብዛት፥ በሀገር ወዳድነትም ይሁን ፥ በጀግንነት ተወዳዳሪ ያልነበረውን የሀገሪቱን የመከላከያ ሠራዊት ፥ የውጊያ ብቃቱንና ወታደራዊ ሥነ ሥርዓቱን ( ዲሲፕሊን) ሊፈታተኑት ካስቻሉት

ምክንያቶች አንዱ፥ የፖለቲካ ካድሬዎች በሠራዊቱ ውስጥ ተሰግስገው ያመጡት ጉዳትና ጥቃት ነው ። የዚህ ውጤት ደግሞ የሀገሪቱን አንድነት ያናጋው ብቻ ሳይሆን፥ ዳር ድንበሯንም ጭምር አስደፍሮ ታሪኳን አዋርዶ ሕዝቧንም ያሳፈረና አንገት ያስደፋ ሆኗል ። የእኛ ዕምነትና ራዕይ፥ የነገዋ ኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ፥ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ የብሔር ድርጅት ቁጥጥር የፀዳና በማንም የፖለቲካ ካድሬ ተውሳክ የማይበክለ ሙያተኛ ተዋጊ ኃይል መገንባት ነው ። በዚህ ለሀገራችን ነፃነትና አንድነት ባለን አቋም ምክንያት ፥ በጠባብ ብሔረኞች ዘንድ " አባይ ኢትዮጵያ " የሚል ምፀት ሲነገርብን ቆይቷል ። ታላቅ ኢትዮጵያ መባላችን የሚያኮራንና የምንደሰትበትም ስለነበረ ዛሬ የወያኔዎችን ምፀት የምንጠቅሰው ፥ በአባይ ኢትዮጵያዊነታችን ፥ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከጥፋት አድነን የነገይቱን ታላቂቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ነው ። አባይ ኢትዮጵያን አስከብረንና አኩርተን በነፃነቷና በአንድነቷ የታፈረች ሀገር መሆኗን ማየት የዓላማችን አልፋና ኦሜጋ ነው ። የጠባብ ብሔረተኞችን የምፀት አነጋገር እንደ ፍሬ-ፈርስኪ የምንቀጥረውም ለዚሁ ነው ።

አስተማማኝና የማይበገር የሀገር መከላከያ ሠራዊት ለመገንባት ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል፥ለዚህ አገልግሎት ዓይነተኞች የሆኑትን የትምህርት ተቋማትን ማቋቋም ነው። ለሀያ አንደኛው ክፍል ዘመን የሚስማማ መከላከያ ኃይል መገንባት ካስፈለገ ለዚሁ ዘመን የሚሆኑ ወታደራዊ ትምህርት ቤቶችና የጦር መኮንኖችን የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ አካዳሚዎች መመስረት የሚያከራክር አይሆንም ። ቀደም ሲል ተቋቁመው የነበሩት ወታደራዊ ተቋማትና አካዳሚዎች ከመፍረሳቸው በላይ ከእነኝህ ወታደራዊ ማስልጠኛ ተቋማትና አካዳሚዎች ሠልጥነው የተመረቁት ወታደራዊ መኮንኖችና ምሁራን በብዛት እንዲጠፉ ተደርገዋል። የአንድን ሀገር የሠለጠነ ወታደራዊ ኃይልና መኮንኖችንም ጭምር ማጥፋት የሚጠበቀው ከቅኝ ገዥዎች እንጅ ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚል ቡድን ባልሆነ ነበር ። በሦስተኛው የዓለም ሀገሮች ተወዳዳሪ ያልነበረው የሐረር ጦር አካዳሚ ፈራርሶ የጎፋያ ማስጫ መሆኑን ማየት፥ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስቆጭም ሆኗል። ለእጩ መኮንኖች ማስልጠኛ ተብለው የተደራጁት ፥ የሳይንስ ላቦራቶሪ መሳሪያዎች ፥ የልብስ ማጠቢያ (ላውንደሪ) ማሽኖች ተነቃቅለው ወደሚሄዱበት ተወስደዋል ። የአካዳሚው መጽሐፍት ቤት ተመዝብሯል ። የአካዳሚው እጩ መኮንኖች እንዲሠለጥኑበት ውድ ዋጋ ተከፍሎባቸው ከውጭ ሀገሮች የተገዙ ምርጥ ምርጥ ፈረሶች በሀራጅ እየተሸጡ ደብዛቸው ጠፍቷል ። ዝነኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይልም ከዚህ አሳዛኝ ዕድል ሊያመልጥ አልቻለም ። ስመ ጥር የነበረው የፖሊስ አካዳሚም ከዚህ የብሔራዊ ጥፋት መአት አላመለጠም ። በአሁኑ ወቅት ስለ ባህር ኃይል አካዳሚ ማውሳት ፥ ልክ በምድር በዳ እንደመጮህ ስለሚቆጠር ጊዜ

ይፍታው ብሎ ከማለፍ የተሻለ አስተያየት መኖሩን እንጠራጠራለን ። ምንም ምን

ተባለ÷የኢትዮጵያን ማንነት ለማጥፋትና የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል ከመጣ የወገን ጠላት በጎ ነገር ስለማይጠበቅ ÷ ያሁኑን ሁኔታ ለመለወጥ ካስፈለገ ÷ ይህን የዘረኛ ሥርዓት አራማጅ ቡድን ከማስወገድ የበለጠ አጣዳፊ ተግባር ሊኖር አይችልም ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነትም ይሁን በእኛም አመለካከት ÷ በሀገሪቱ አንጡራ ሀብትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የተቋቋመ የመከላከያ ሠራዊት ÷ በመሠረቱ ሊሆን የሚችለው የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ነው ።በአጠራርም ይሁን በአተረጓጎም÷ በአገልግሎትም ይሁን በታማኝነት የሙያ ግዴታውን የሚወጣው ለሀገሩ እንጅ ለማንም የብሔር ድርጅትም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም ። የዚህም ቀጥተኛ አስተጋብዖ ተጠያቂነቱና ኃላፊነቱ ÷ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ እንደሆነ ያርጋግጥለታል። ይህም በበኩሉ÷የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል እንጅ÷ በየጊዜው ለሚፈራረቁ አምባገነን ሥርዓቶች መሳሪያ እንዳይሆን ያግደዋል። ምንም እንኳን÷ ደርግ የራሱን የጭካኔ አገዛዝ ለማራመድ ሲል በአብዮት ስም የነበልባል ቡድን አቋቁሞ ብሄራዊ ወንጀል ሲፈጽም እንደነበረ ሁሉ ÷ ዛሬም ወያኔ ሕዝብ የሚጨፈጭፍበት የአጋዓዚ ጦር መስርቶ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የሚያካሄደውን የግድያ ወንጀል መፈፀሙ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሸሸገ ባይሆንም ÷ ሌላው ተዋጊ ሠራዊት ግን የወገኑን ደም በጭካኔ እንደማያፈስስ ጠንቅቆ ሊገነዘብ ይገባዋል ። የሀገሪቱን ዳር ድንብር ለመጠበቅ ሲል ደሙን እያፈሰሰ አጥንቱን እየከሰከሰ ከውጭ ጠላት ጋር መፋለም የሚገባው ተዋጊ ሠራዊት ÷ ከሀገሩና ከሕዝቡ ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ÷ የመሳሪያውን አፈ ሙዝ ወደማን እንደሚያዞር በሚገባ ማወቅ አለበት ። የመከላከያ ፖሊሲያችን አፅንዖት ከሚሰጣቸው ዐበይት ጉዳዮች መካከል÷ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ÷ የሀገሩን ሕገ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ÷ የዓለምአቀፍ ደንቦችንና ህግጋትን መረዳት የሚያስችለውን በቂ ትምህርት እንዲያገኝ ማድረግ ይሆናል ። የኢትዮጵያ የመከላካያ ሠራዊት ሃያ አንደኛው ክፍል ዘመን የሚጠይቀውን ሁለንተናዊ የወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀትና ጥበብ ማግኘት እንዳለበት ከልብ የምናምነበት ታላቅ ቆም ነገር ነው። አ ! ጊዜ ለኩሉ ወይም ለሁሉም ጊዜ አለው እንዲሉ ግን የዛሬ ዋናውና ቀዳሚ ግዳጃችን የወያኔን አገዛዝ ገርስሶ ማስወገድ ነው። ይህም ግዳጅ የወያኔን የአፈና ኃይልና ጦር በዕይታ አስገብተን ማቸነፍም ማሸፈትም መቻልን የግድ ይላል ።